# ወያኔ እንበልተው!

**(ከእስከ ነጻነት)**

የወያኔ አባላትን ሁሉ በአንድ ቅርጫት ውስጥ መክተትና በአንድ አይን መመልከት፣ በአንድ ሚዛን መለካት ስህተት ነው እላለሁ: ወያኔን በባህሪያቱ መከፋፈልና በብልት ከፋፍሎ መመልከት ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አለው:

1. የወያኔን አባላት በጅምላ እንደጠላት ከመቁጠር ማ ምንድነው? ተግባሩና ምግባሩስ ብሎ ምክንያታዊ ወቀሳ፣ ከሰሳና ትችት ለመስጠት ያስችላል
2. የትግል ኃይላችንንና ስልታችንን ኢላማ መምታት በሚያስችል (Target oriented) መልኩ መቀየስ እንችላላን:
3. የትግል አጋር ሊሆኑ የሚችሉ የወያኔ አባላትን ለመለየትና በትግሉ ለማሳተፍ ያስችለናል:
4. የፍርድ ቀን እየቀረበ ስለሆነ እያንዳንዱ ቀለበት ወይም ክበብ የሚጠየቅበትን ወንጀል በፈርጅ፣ በፈርጁ ለመለየትና የክሱን ጭብጥ በመረጃ ለማጠናከር መረጃ የማሰባሰቡንና የማጠናቀሩን ሂደት ያቀልልናል:
5. የወያኔ አባላት ራሳቸው በየክበቡ፣ ቀለበቱ ምን እየተደረገ እንደሆነ ለማወቅና ቆም ብሎ ነገሮችን ለማጤን እድል ይሰጣቸዋል::

ወያኔን መበለት ከመጀመሬ በፊት ስለ ወያኔ አባል አመላመልና የአባላቱን መብትና ግዴታ ጠቆም አድርጌ ልለፍ: ወያኔ የትግራይ አባላቱን እንዴት እንደሚመለምል ትግራይ ውስጥ መሆን ወይም የወያኔ አባል መሆን አያስፈልግም:፡ የዩኒቨርሲቲና የኮሌጅ ምሩቃንን የኢህአድግ አባል ካልሆናችሁ ስራ አታገኙም እንደሚለው ሁሉ: የወያኔ አባል ያልሆነ ትግሬ ደግሞ ስራ፣ ነጻ የውጭ የትምህርት እድል: ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች ማጣት ብቻ ሳይሆን የዜግነት መብቱንም ሊያጣ፣ ሊታሰር፣ ሊገረፍና ሌላም ሊደርስበት እንደሚችል መገመት አስቸጋሪ አይመስለኝም። ይህ ደግሞ ሁሉም የወያኔ አባል ወያኔን ይደግፋል፤ የወያኔ አመረር አስደስቶታል የሚለውን አባባል አያጠናክርም። በሚልዮን የሚቆጠሩ አባላቱ በሙሉ ህሊናቸውን ሸጠዋል ወይም ስተዋል ማለት ከሐቅ መራቅ ይሆናል:፡ በጣም የሚያሳዝነውና የሚያስገርመው ግን የሰራዊቱ አባላት ሁሉ የድርጅት አባል ናቸው:፡ ይህን መነሻ በማድረግ ወደ ብልት ማውጣት ልሂድ::

በኔ አመለካከት ወያኔን በሦስት ባህሪያት ከፍዬ፣ በልቼ እመለከተዋለሁ፡-

1. ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ማጥፋት
2. የትግራይን ክልል ከሌሎቹ ክልሎች መለየት
3. የአገርንና የህዝብን ሐብት መዝረፍ:

ስለያንዳንዱ ብዙ የተባለ ስለሆነ በዚህ አንባቢን ላሰለች አልፈልግም:፡ ለዚህ ጽሑፍ እንዲያገለግለኝ ብቻ በአጭሩ አስቀምጣቸዋለሁ

1. ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ማጥፋት: ስር ከሚጠቃለሉ ተግባሮች ጥቂቶቹ፡-
   - የባህር በር ማሳጣት
   - ከጎረቤት ሐገሮች ጋር ሰላም እንዳይኖር ግጭት ሊያስነሱና ወደፊትም ሰላም ለማስፈን አስቸጋሪ የሚሆኑ ሁኔታዎችን መፍጠር:፡ ለምሳሌ: ከኤርትራ ጋር የለ ያልተቋጨ የድንበር ጉዳይ፣ ከሱዳን ጋር መሬት በመስጠቱና ወደፊት ለሚነሳ የይገባኛል ጥያቄ፣ ከሱማሌ ጋር በማያገባው የውክልና ጦርነት ምክንያት:
   - ህዝብን ጸጥ ለጥ አድርጎ ለመግዛት ጅምላ ጭፍጨፋ ማካሄድ: (ዘር ማጥፋት) ማሰርና ማሰቃዬት፣ ሰብዓዊ መብቶችን መግፈፍ:
   - ህዝብን በቋንቋ በመከፋፈልና መግባቢያና መገናኛ ድልድይ ማሳጣት:
   - በህዝቡ ስም በርዳታ የተገኘውን፣ ቀጣይ ትውልድ ያለእዳው እንዲከፍል ተውስኖበት በብድር የሚገኘውን ገንዘብ እየዘረፉ በውጭ ባንክ ማከማቸት:

2. የትግራይን ክልል ከሌሎቹ ክልል መለየት ስር ከሚጠቃለሉ ተግባሮች ጥቂቶቹ
   - ለትግራይ ክልል ልማት የሰጠውን ያህል ትኩረት ለሌሎች ክልሎች ያለመስጠት:
   - ከሌሎች ክልሎች ለም መሬት ቆርሶ ለትግራይ መስጠት:

- ፖሊቲካውን፣ ኢኮኖሚውን፣ ጦር ኃይሉን በሙሉ በትግራይ ተወላጆች ቁጥጥር ስር ማድረግ:
- የትግራይን ህዝብ የተለየ አድርጎ መመልከት:

3. ያላግባብ ብልጽግናና ዘረፋ ስለዚህ ብዙ የተባለ ሰለሆነ እኔ አልደግመውም:

**የድርጅቱ መዋቅር ምን ይመስላል**

በኔ እይታ: የድርጅቱን አወቃቀር እንደ ባህሪው በሦሥት ቀለበቶች የተዋቀረ ተደርጎ ለታይ ይችላል:

1. የውስጥ ቀለበት (Inner circle) በመለስ፣ በረከት፣ ስብኃት የሚመራ ከላይ ለተጠቀሱት ተግባራት ሁሉ ምንጭ: በተለይም ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን በማጥፋት ብቸኛ ተጠያቂ ይህ ክፍል ነው እላለሁ: በቀለበት ሁለትና ሶስት ያሉት አባላት በወንጀሉ ተባባሪ ቢሆኑም ሁሉም፣ ሙሉ በሙሉ የሐገርን መጥፋት ይደግፋሉ ብሎ ማለት ከእውነታ መውጣት ይመስለኛል:፡ ሐገር በማጥፋት ወንጀል ተግባር የተፈጸሙ ብዙ ወንጀሎች በቀጥታ በነዚህ አባላት ቀጥተኛ ትእዛዝ የተፈጸመ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል:፡

   ለአብነት የ1997 የአዲስ አበባ ጭፍጨፋ የተካሄደው በመለስ ቀጥተኛ ትእዛዝ የሆነበት ምክንያት ከሱና ከክበብ አባላቱ ውጭ ህዝቡን በጅምላ ጨፍጭፍ ብሎ ትእዛዝ ለመስጠት የሚደፍር አካል የለም ብሎ በማመኑ ነው:፡ የአዋሳ ጭፍጨፋ በበረከት ስምኦን ትእዛዝ መፈጸሙንም ልብ ይሏል:፡ ለሱዳን መሬት ተቆርሶ ሲስጥ ያወቀ አልነበረም:፡ ብዙ ነው ግን ሁሉም ስለሚታወቅ ይብቃኝ::
2. ሁለተኛ ዙር ቀለበት: በቀለበት አንድ ውስጥ ያሉትንና ለሎች አባላት ጨምሮ በቁጥር 2 (የትግራይን ክልል ከሌሎች ክልሎች መለየት) ለሚለው ተግባር ፈጣሪና ለተግባሩም አስፈጻሚዎች ናቸው: ይህ ተግባር ሲፈጸም ደግሞ የሌሎች ክልል ህዝቦች መብት ተጥሷል፣ ሰብዓዊ መብት ተረግጧል፣ ወንጀል ተፈጽሟል:
3. ሦስተኛ ዙር ቀለበት ውስጥ ያሉ ከላይ በቁጥር አንድና ሁለት ያሉትን ጨምሮ በወያኔ አባልነት የተመዘገቡትን በሙሉ የሚያጠቃልል ነው:፡ በዚህ ቀለበት ውስጥ፣ (ቀለበት አንድና ሁለትን ሳይጨምር) ያላግባብ ለመክበር፣ ለለት ኑሮ ለተሻለ ህይወት ብለው የተደባለቁ: ወያኔ በርግጥ እንደሚያወራው ለሰላምና ለዲሞክራሲ የቆመ መስሏቸው የገቡ፣ በአንድም ይሁን በሌላ የወያኔ አስገዳጅነት የተደባለቁና አሁን መውጫ አጥተው በህሊና እስረኝነት የሚኖሩትን ሁሉ ያጠቃልላል: አብዛኛው ህዝብ እንግዲህ በዚህ ቀለበት ውስጥ ነው ማለት ነው:

**የወያኔ አባላት ነጻ ናቸው ወይ?**

ወያኔ የትግራይን ህዝብና አባላቱን በሶስት ዋና፣ዋና መንገዶች ይቆጣጠራል

1. **እንደ ብረት በጠነከረ የስለላ መረብ:** የሰለላ መረቡ እንዴት የኢትዮጵያን ህዝብ ተብትቦ እንደያዘው ሁላችንም የምናውቀው ነው: ለትግራይ ህዝብ እና ለአባላቱ የዘረጋው መረብ ደግሞ ከብረት የጠነከረ መሆኑን መረዳት አስቸጋሪ አይመስለኝም:፡ በቀላሉ ብንመለከት በጫጉላ ጊዜው የመጻፍ መብት ተፈቅዷል ብሎ የመሐል አገር ህዝብ ከግል ጋዜጦች አንዳንድ መረጃዎችን ሲቋደስ ትግራይ ከወያኔ መጽሔትና ጋዜጣ በስተቀር አንድም የግል ጋዜጣ ወይም መጽሔት አይገባም ነበር:፡ የወያኔ አባላቶቹም እንዲያነቡ አይፈቀድም ነበር:

2. **በፕሮፓጋንዳ ዘመቻ:-** ላለፈው 35 ዓመታት የትግራይን ህዝብና አባላቱን ህውሃት ብቸኛ ለትግራይ የቆመ ድርጅት መሆኑን፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ የትግራይ ተወላጆችን ሥጋ ለመቀራመት አሰፍስፎ የሚጠብቅ አውሬ መሆኑና ለትግራይ ህዝብና የወያኔ አባላት ያላቸው ብቸኛ አማራጭ ከወያኔ ቁንጮ የሚያፈሱለትን ትእዛዝ ብቻ እየተቀበለ የራሱንና የኢትዮጵያውያንን ደም ማፍሰስ እንደሆነ ሲሰብኩት የኖሩት ጉዳይ ነው: ይህ ደግሞ ቀላል የማይባል ስነ ልቦናዊ ጫና እንደፈጠረባቸው እንገነዘባለን:

3. **በጥቅም መያዝ**: ይህንን አቶ ሚካኤል ሐገር ሳትሰበር ዝምታ ይሰበር በሚል አርዕስት (http://www.ecadforum.com/files/yetigrayhizb.pdf) በሚገባ ሰለገለጹት አልደግመውም ብዙም ተብሎበታል:

እንዲሚታወቀው የወያኔ አባልነት እንድ ዕጽ አዘዋዋሪ ወይም ማፊያ ቡድ የእድሜ ልክ አባልነት እንጂ አልተስማማኝም ተብሎ ለቆ የሚወጣበት ድርጅት አልመሰለኝም:: አንድ አባል ድርጅቱን ለቆ መውጣት

የሚችለው፡ የውስጠኛው ቀለበት በራሱ ምክንያት ሲያባርረው፣ ሲሞት፣ ሲታሰር ወይም ከሐገር ሲሰደድ ብቻ እንደሆን ይሰማኛል፡፡ ሐገር ጥሎ የተሰደደ የወያኔ አባልም ቢሆን ያለው ዕድል አርፎ፣ አፉን ዘግቶ ተደብቆ መኖር ነው፡፡ ልቃወም ካለ የገዳይ ቡድን ይላክበታል፡፡ ይህን ደግሞ ሩቅ ሳንሄድ በታምራት ማየት ይቻላል፡፡ ከእስራት ተፊቶ፣ ከሐገር ተሰዶ እንኳን ለምን እንዳሰሩት መናገር አልደፈረም፡፡ ያውም ክርስቶስን ያህል ጠባቂ እያለው፡

የትግራይ ህዝብ ወይም ሁሉም የወያኔ አባላት የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያዊነት መጥፋት፣ የትግራይ ህዝብ የተለየ ተደርጎ እንዲፈረጅና ከሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች እንዲለይ መደረግ፣ የሐገር ንብረት መመዝበርን ይደግፋሉ ብሎ ለማለት አይቻልም፡፡ በግልጽ ወያኔን ለመቃወም ግን ከላይ የጠቀስኳቸው ጫና ፈጥሮባቸዋል ብዬ አስባለሁ፡፡ ይህ ቢሆን ደግሞ ሊገርም አይገባም፤ አብረዋቸው የነበሩና የነመለስን እኩይ ምግባርና ተግባን የተቃወሙ የትግል ጓዶቻቸው ላይ የደረሰው ሁሉ በዓይናቸው አይተነዋል፣ ኃዘኑንም አስተናግደዋል፡፡
ሌላው ደግሞ 35 አመት በዘለቀ የጥላቻ ዘመቻ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ወገኔ ብሎ አይቀበለኝም የሚል ሌላ የፍራቻ አድማስ ፈጥሮላቸዋል፡፡ የተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብም (ሁሉም ባይባልም) እጁን ዘርግቶ ልቡን ከፍቶ ለመቀበል የተዘጋጀ አይመስልም፡፡ ቢያንስ እስካሁን፡ እንግዲህ የትግራይ ህዝብና የወያኔ አባላት እንደዚህ ባለ፣ ማምለጫው በጠበበ ችግር ውስጥ ናቸው ማለት ነው፡፡

እንዲዚያም ሆኖ የትግራይ ህዝብ ባገኘት ጠባብ እድል ወያኔን የማይደግፍ መሆኑን አሳይቶናል፡ ቅንጅት መቀሌ ስብሰባ ያካሄደ ጊዜ አዳራሽ ጠቦ እንደነበር፣ በቅርቡም የአረና ትግራይ ስብሰባ ጊዜ የታየው ሁኔታም ምስክር ነው፡፡

ይህን የሸር መረብ ለመበጣጠስ የትግራይ ህዝብና የወያኔ አባላት እንዲሁም የተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ ማድረግ ያለበት፡-

- የኢትዮጵያ ህዝብ የትግራይን ህዝብም ሆነ የወያኔ አባላትን (ሐገር በማጥፋትና ዘር ባማጥፋት ወንጀል የተሳተፉትን ሳይጨምር) እንደወገኑ እንጂ እንደ ጠላት ወይም ባላንጣ የሚመለከተው አለመሆኑን ማሳወቅ፣ ማስረዳት፣ ማወቅ፣ መረዳት፤
- ከወያኔ መረብ አምልጠው የሚመጡ አባላትን ለወያኔ ጥቃት እንዳይጋለጡ ከጎናቸው እንድንቆምና ይህንንም እንዲያውቁ ማድረግ፤
- ከወያኔ አፈንግጠውው የመጡትን ሁሉ ሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ እጁን ዘርግቶ ልቡን ከፍቶ እንዲቀበላቸውና ይህም እንዲረጋገጥላቸው፤
- አንድ ህዝብ እንጂ ወያኔ እንዳስቀመጠው ሁለት ህዝብ አለመሆናችንን ሁላችንም መረዳትና ለወደፊት የሐገራችን እጣ ፈንታ ለማሳመር በጋራ አገራችንን የማዳን ተግባር አብረን እንድንተልም፤
- የትግላችንን ኢላማ ቀጥታ መርዙ ላይ ማድረግና ከነሰንኮፉ መዞ ለመጣል በጋራ መስራት፤
- የወያኔን አባላት በየፈርጃቸው መመደብና ለያንዳንዱ ፈርጅ ስልታዊ የሆነ የትግል ዜዴ ማደራጀት፤
- ከትግራይ ክልል ውጭ በተለይም በውጭ ሐገር ያላችሁ የትግራይ ተወላጆችና ምሁራን ያላችሁን ቅሬታም ይሁን አስተያየት፣ የትግራይ ህዝብ ያለውን ሐሳብ ብታጋሩን ጥቅሙ የጋራ ይሆናል።

እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይጠብቅ